# ፅናት

ሥርጉተ ሥላሴ

አውራ! ወጋግራ! ዓምደ ብራ የሚያበራ የሚገራ ፍርሃትን ስጋትን ጭንቀትን የሚመክት። የውስጥ ደም ፈተናን የመቋቋም አቅምን፤ ብቃትን፤ ልኬታን የሚበይን ክቡር ሥነ ምግባር ነው። አጥንትን ስርስሮ የሚፈትሽ። እራስን በእራስ የሚዳኝ።

መብላትም መጠጠትም፤ ድሎትም መከፋትም፤ መኖርም ማለፍም ሁሉም በጊዜያቸው መዋ ዕለ ዕደሜያቸውን ተክዘው ይበናሉ ይተናሉ። የሕይወት ኾንጉርጉር ገጠመኝም እንደ ዕጣ ፋንታው ሊመንን ወይ ሊመነኩስ ወይም ዓለምን መስሎ ሊያድር ይችላል።

ሀገራዊ ብቃትን የሚመዝኑ ችግር እና መከራን ተቋቁሞ ለሚያልፍ ዕድሜ፤ ለዕልፍ የደም ዕንባ  ዕልፍ ብሎ ሃሳርን  በፀጋ እና በሃሴት መቀበል፡ አልፎ ተርፎም ሞትን ቅደመኝ ብሎ በቃል መፅናት ግን የሰንደቆቹ ሁሉ ጉልላት ነው።

ቃል ቃል ነው። ቃል ቃልነቱ ቃል ሆኖ ፋና የሚሆነው ግን ቃል አሳለፊው ለቃል ኪዳኑ ሲያደገድግ ሲደሰግድ ቃሉን ለቃሉ በተግባር ሲያሰጌጥ ብቻ  ይሆናል።

ይህ ደግሞ የሁለመናን ከብረት የተሰራ ፅናትን ይጣይቃል። ወጀብ፤ ዓውሎ፤ ጎርፍ ሳያሸንፈው፡ እንደ እንሰሳ ለከርስ ሳያድሩ መፋለምን፤ መቁረጥን፤ መወሰንን ይጠይቃል። ግለኝነትን ድል ነስቶ ለሚሊዎን ብሶት ዘብ መቆምን ይጣይቃል እራስን ይፈትናል ያፋጥጣል።

*

<u>ፅናት</u> ታማኝነትን አፍልቆ መሆን መቻልን ይገብራል። ግልብ ሰራሽን ውስጥነት አንጠሮ ምልከት ዓርማ ይሆናል። የሴልን የነርብን የጅማትን ህዋስ እንደ ወረቅ ያነጥራል። የመስዋትነት ቃና ዘጉባኤ ይሆናል።

ፅናት ማንነትን አጉልቶ እራስነትነ ይተርጉማል። ከዘማናችን ብርቱ፤ ጠንካራ፤ ታታሪ መሪዎች አንዷ ብረቋ ከሆኑት ከጀግናዋ ዳኛ ብርቱከን ሚዲቅሳ ያገኘነው ዘመን የማይሽረው፤ ወቅትታት የማያ-ወይቡት፤ ጊዜ የማያፋድስው የሀቅ እንክብል ይህ ነው።

ስለሆነም  ትውልድ ለማይተካቸው ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር በተግባር ያጌጠ መከራን በፍቅር ተቀብሎ ላሰተናገደ ጀግንነታቸው አቻ የለሽ ፅናታቸው ..... የመታገያ የጋራ ዓርማችን ነው።

ጀግንነት ፋሽስትን ድል ነሰቶ ህዝባዊ ፍቅርን በምዕላት በእያንዳንዳችን ህሊና ሲከትም በእድሜዬ ያዬሁት በክብርትነታቸው ነው። ስለሆነም „ውረሰ ጽናትን“ በልቦናዬ አብቅሎ ያለማ ዘንድ መደህኔዓለም አባቴን ተንበርክኬ በአፅህኖት እለምነዋለሁ።

ክብርተ ዳኻኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር  የቃል አርበኛ፤ የቃል አብየተኛ፤ የቃል ሁነኛ፤ የቃል አሥራት፤ የጽናት ጉልላት የተናገሩትን ሆነው የተገኙ የእኩልነታችን  ሰነደቅ ፋና ወጊ ናቸው።

በውስጤ ያለው የፅናት ራዕይ በክብረትነታቸው ዙሪያ ቋሚ የሆኑ ተግባራትን ያካትታል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በሲዊዘርላንድ በዙሪክ ከተማ ራዲዮ ፐሮግራም መጀመር ነው። በሌላ በኩል በድህር ገጹም የተገባውን ያህል አትኩሮት መስጠት። …

ካለ ሴቶች ንቁ እና ብረቱ ተሳተፎ የፀረ ወያኔ ትግሉ ዓላማ እግቡ አይደርስም!
ወርቅን ያነጠረ ፅናት የዕድሜ ልክ ዕንቁ ነው!
ነፃነት በወያኔ እስር ለሚማቅቁት  ለክብርት ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር እና  በወይኔ እስር ለሚመቅቁ ወገኖቻችን ሁሉ!
ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!